የተቀናጀ የቤተሙከራ አገልግሎቶች ክፍል ሪችሞንድ፣
ቨርጂኒያ
**ለታካሚዎች የሰገራ አሰባሰብ መመሪያ**

## <u>የሰገራ መሰብሰቢያ መሳሪያ ይዘት፡</u>

- ሶስት (3) – 8 x 10 ፕላስቲክ ባዮሀዛርድ ናሙና ከረጢቶች
- አንድ (1) - ቀይ ፈሳሽ ያለው ትቦ
- አንድ (1) - ባዶ ኩባያ
- አንድ (1) - የሚጣል መቆንጠሪያ
- አንድ (1) – DCLS ማስተላለፊያ ፎርም
- አንድ (1) - የመሰብሰቢያ መመሪያ ፎርም
- አንድ (1) - የወረቀት ሰገራ መሰብሰቢያ መሳሪያ
- ሁለት (2) - የትቦ ላይ ጽሁፎች

**<u>የሰገራውን ናሙና መሰብሰብ፡</u>** (ስእሎችን ለማየት ከጀርባ ያለውን ይመልከቱ)


1. ቀጥሎ ያለውን የ DCLS ክሊኒካዊ ማይክሮባዮሎጂ/ቫይሮሎጂ መጠየቂያ ፎርም ይሙሉ፡

| A. የታካሚው መረጃ ሳጥን | B. የታካሚ ጤና ታሪክ ሳጥን | C. የጀርባው ገጽ ራስጌ |
|---|---|---|
| 1. የእርስዎ ስም 4. ጾታ<br>2. የልደት ቀን 5. አድራሻ<br>3. እድሜ 6. ዘር/ብሄር | 1. የታዩ ምልክቶች<br>2. ምልክቶች መታየት የጀመሩበት ቀን (የጅማሬ ቀን) | 1. የእርስዎ ስም<br>2. የልደት ቀን |

2. እስክቢርቶ ወይም ማርከር በመጠቀም፣ ስምዎትን፣ የልደትዎን ቀን እና በመጸፊያው ላይ ያለውን የተሰበሰበበትን ቀን እና ቦታ ማለትም በባዶው ኩባያ እና ቀይ ፈሳሽ ያለበት ትቦ ላይ ይጻፉ።
3. ሰገራ ከመሰብሰብዎ በፊት በመጀመሪያ ሽንትዎን ይሽኑ ይህም ሽንት ከሰገራው ጋር እንዳይደባለቅ ለማድረግ ነው። ሰገራ በሚሰበሰብበት ወቀት ሽንትዎን አይሽኑ። ከሰገራው ጋር ውሀ፣ ሶፍት ወይም ሳሙና አይደባልቁ።
4. ሰገራው ኢንፌክሽን ሊያሰራጭ የሚችሉ ጀርሞች ሊኖርበት ይችላሉ። **ሰገራ መከሰብሰብዎ በፊት እና በኋላ እጅዎትን መታጠብዎን አይዘንጉ።**
5. የወረቀት ሰገራ መሰብሰቢያ መሳሪያውን ጠፍጣፋ በሆነው ቦታ ላይ ያድርጉ ከዚያም የጎኖቹን ክንፎች ይጠፉ።
6. በመሰብሰቢያው እቃ ላይ ያለውን የሚያጣብቀውን ማጣበቂያ ይላጡ።
7. የተጋለጠውን ማጣበቂያ በመቀመጫው የላይኛው ክፍል ላይ ያድርጉ። መሰብሰቢያው መሳሪያ ከመቀመጫው በታች እንደተቀመጠ እርግጠኛ ይሁኑ።
8. የመሳሪያውን መከካል በመጫን ጎድጓዳ ቅርጽ ይስሩ። በጎድጓው ቅርጽ ውስጥ ሰገራዎን ያስገቡ። በመሰብሰቢያው ውስጥ ሽንት አንደማይገባ እርግጠኛ ይሁኑ።
9. ባዶ የሆነው ኩባያ ውስጥ ሰገራውን ለማስተላለፍ መሳሪያው ውስጥ ያለውን መቆንጠሪያ ወይም ቀይ ፈሳሽ ያለበትን ትቦ ጥቅም ላይ በማዋል ባዶው ኩባያ ውስጥ ያስተላልፉ። ሰገራ መሰብሰብ ያለበት ከመሰብሰቢያው እቃ ውስጥ ብቻ ነው። ከሽንት ቤት መቀመጫው ውስጥ በምንም አይነት መንገድ አይቆንጥሩ። ኩባያውን ከ ½ እስከ ¾ ይሙሉት። ከመጠን በላይ አይሙሉት። ግጣሙን ጥብቅ አድርገው ይግጠሙት።
10. መምጠጫ ጨርቅ ባለው የ ፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ሰገራው ያለበትን ኩባያ ይክተቱት። ጀርባው ላይ ያለውን ያላቁ እና ማጣበቂያውን ገልጠው ሰማያዊውን ማጣበቂያ በመጫን ከረጢቱን ለመዝጋት ጥቅም ላይ ያውሉ።
11. ከአንድ ጥቅም በኋላ የሚጣለውን መቆንጠሪያ ወይም ቀይ ፈሻሽ ያለበትን ትቦ ሰገራውን ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ ያውሉ። በመያዣው ውስጥ ያለው ቀይ ፈሳሽ ሞልቷል የሚለው ምልክት ላይ እስከሚደርስ ድረስ ኩባያውን ይሙሉት። መክደኛውን በደንብ አድርገው ገጥመው ይዝጉት። ቀይ ፈሳሽ ያለውን ትቦ መምጠጫ ካለው ከሁለተኛው የፕላስቲክ ከረጢት አጠገብ አድርገው ይክተቱ። ከጀርባ ያለው በማንሳት እና ሰማያዊውን ማጠበቂያ በመጫን ከረጢቱን ይዝጉ።
12. ሰገራው ያለባቸውን 2 ከረጢቶች በሶስተኛው ከረጢት ውስጥ ይክተቱ። በፊተኛው ኪስ ውስጥ አረንጓዴውን የማስተላለፊያ ፎርም ያስገቡ እና ግጣሙን ይዝጉ።
13. የሚቀረውን ሰገራ የያዘውን ከረጢት አራቱን የማጣበቂያ ነጥቦች በማላቀቅ ያስወግዱ። የሚቀረውን ሰገራ እና መያዣ ያስወግዱ።
14. የመሰብሰቢያውን መሳሪያ እና ካርድ ቦርድ ያስወግዱ። የመሰብሰቢያውን መሳሪያ እና መቆንጠሪያውን ማንኪያ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ይጣሉ። **እጅዎትን በደንብ አድርገው ይታጠቡ።**


## <u>መጠቅለል፣ ማስቀመጥ እና ማንሳት፡</u>

**1.** 2 የሰገራ ማስቀመጫዎች ያሉት ከረጢት በማቀዝቀዣ ውስጥ ሊቀመጥ ያስፈልጋል ይህም በጤና ዲፓርትመንት ለመውሰድ ዝግጁ እስከሚሆን ድረስ ነው። **<u>ናሙናዎቹን አያድርቁ።</u>**
2. ናሙናዎቹ ለመወሰድ ዝግጁ በሚሆኑበት ወቅት ወይም ምንም አይነት ጥያቄ ከመሰብሰብ ጋር በተያያዘ ካለዎት አካባቢያዊ ጤና ዲፓርትመንትዎን ያግኙ።





1

- የ DCLSን ክሊኒካዊ ትክክለኛ ማይክሮ ባዮሎጂ/ቫይሮሎጂ መጠየቂያ ፎርም ይሙሉ።
- ስምዎትን፣ የልደት ቀንዎን እና ናሙናው የተሰበሰበትን ቀን ሁለቱም **መያዣዎች ላይ ይጻፉባቸው**።




2

መሰብሰቢያውን መሳሪያ ጠፍጣፋ በሆነ ቦታ ላይ ያድርጉ እና **እጀጌዎቹን ይዝጉ**።




3

በሁለቱም ጎኖች ላይ ያለውን **ማጣበቂያ ላይ ያለውን መከላከያ** ይላጡ (ሰማያዊ ክፍሎቹ ላይ)



4

- **መሰብሰቢያውን በሽንት ቤት መቀመጫው ውስጥ ያስገቡ** ይህም ወደ መጨረሻው ክፍል ማለት ነው በሽንት ቤት መቀመጫው ላይ የተጋለጠውን ማጣበቂያ ያያይዙ። መሰብሰቢያው መሳሪያ ከሽንት ቤት መቀመጫው በታች እንደሆነ ሊያረጋግጡ ያስፈልጋል።
- መሰብሰቢያውን መሳሪያ በጎድጓዳ ቅርጽ ያጎድጉዱ።
- በሰሀኑ ውስጥ ሰገራውን ያስገቡ። **የሚከተለውን አያደርጉ** በጎድጓዳው ውስጥ ሽንትዎን መሽናት።




5

- በመሳሪያው ውስጥ ያለውን የቆሻሻ መጣያ ጥቅም ላይ በማዋል፣ ከሰሀኑ ላይ **ሰገራውን ያንሱ** እና ባዶ የሆነው ሰሀን ውስጥ ያስገቡ። ኩባያውን ከ ½ እስከ ¾ ይሙሉት። ከመጠን በላይ አይሙሉ። **አጥብቀው መክደኛውን ይዝጉ።**
- ራሱን መቆንጠሪያ ጥቅም ላይ በማዋል፣ ሰገራውን ከመሰብሰቢያው ላይ አንስተው ከቀይ ፈሳሹ ባለበት ትቦ ውስጥ ያስገቡ። ትቦው ውስጥ “የመሙያው መስመር” ድረስ ያስገቡ። ከመጠን በላይ አይሙሉ። **አጥብቅ ይግጠሙ** እና በደንብ አድርገው ይደባልቁ።

6

- ሰገራ ብቻ ያለበትን ናሙና በትልቅየው የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ያስገቡ። ቀጭኑን ልጥፍ አንስተው ማጣበቂያው እንዲታይ ያድርጉ እና ሰማያዊውን በመጫን ይግጠሙት። ምንም አይነት አየር በከረጢቱ ውስጥ እንደማይገባ እርግጠኛ ይሁኑ።
- ሰገራው ያለበትን እና ቀይ ፈሳሽ ያለበትን ትቦ ለብቻው በከረጢት ውስጥ ያስገቡ።
- 2 ቱንም የተዘጉ ከረጢቶች አንድ ላይ አድርገው በሶስተኛ የፕላስቲክ ከረጢት ውስጥ ያስገቡ። የተጠናቀቀውን **አረንጓዴ የ DCLS ፎርም** በፊተኛው ኪስ ውስጥ ያስገቡ እና እጅጌዎቹን ይጠፉ።
- የሰገራ ናሙናው ያለበትን ከረጢት ፍሪጅ ውስጥ ይክተቱት። **አያድርቁት።**
- ናሙናው ከእጅዎ ላይ እንዲነሳ አካባቢያዊ የጤና ዲፓርትመንትዎን ያግኙ።